የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች የሚያደርጉትን ጸረ-ወያኔ ፕሮፓጋንዳ፣ቅስቅሳ፣ አስተምሮት፣የህዝብን ንቃተ-ኅሊና ለማሳደግ የሚረዱ ከራሳቸው ከድርጅቶችም ሆነ ከአባሎቻቸውና ከደጋፍዮቻቸው የሚፈልቁትን የጥናት ጽሁፎች ወደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጆሮ፣ዓይንና አእምሮ ለማድረስ የራሳቸው የሆነ ፦የቴለቭን፣የሬዲዮና የኅትመት ዜና አውታሮች/ሚዲያ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ።ቢያንስ ቢያንስ አገር ቤት የሚዘልቅ አንድ ሁነኛ ቴሌቫይዝድ ሬዲዮ እና ለዲያስፖራው ዓለም የሚያገለግ አንድ ሁነኛ የኅትመት ዜና አውታር (print media) ያስፈልጋቸዋል። ያ ካልሆነ ልፋታቸውና ጥረታቸውን ከላይ የጠቀስኳችው፣ የሚዲያ ጉልበት( multi-media power) ባካበቱ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ተኮርዦውና በቃላት ኮስሞቲክስ ሸፋፍነው ፣የራሳቸው/የእነርሱ የጭንቅላት ምርት(intellectual property) አድርገው ይጠቀሙበታል። ምክንያቱም ኢትዮ-ዲያስፖራ ዜና አውታሮች (media)የምሁራን የጭንቅላት ምርት ሕግ (intellectual property law) ያለቸው  አይመስለኝም ፤ ቢኖርም በጣም የላላ ወይም ለዘፌር ዓይነት (Laissez-faire type) እንደሆነ እገምታለሁ

በዚህ ወቅት የዚህ ዓይነት የሚዲያ አቅም ያለው ግንቦት ሰባት (ግ7) ብቻ ነው ፤ሁላችንም እንደምናውቀው ፣ ግንቦት7  የእሳት ቲቪ፣የሳት ራዲዮ፣የወቅታዊ ጉዳዮች፣ኢትዮጵያውያን ኮምኒቲ ዲሞክራሲያዊ መድረክ፣አባይ ሚዲያ፣ተንሳ ሬዲዮ (Esat TV,Esat Radio,Current Affairs ,Ecadf,Abaye Media,Tensae radio/) ባለቤት ነው። የማላውቃቸውም ሊኖሩት ይችላሉ፣ በሌሎች ኢትዮ-ዲያስፖራ ዜና አውታሮች/ሚዲያ ባለቤቶች ላይም በቀጥታም ሆነ በኢ-ቀጥታ ተጽኖ ማድረግ ችሎዋል፤ ማለት የነዋይ ድጎማ በመስጠትና ግንቦት7 ከተቃወምክ /ከተቃወምሽ ወየውልህ/ልሽ !በማለትም።

ግንቦት7 የኢትዮ-ዲያስፖራ ሚዲያ ፈጣሪ እንጂ ለሌሎች ኢትዮ-ዲያስፖራ ሚዲያ ባለቤትች ተለማማጭ  አይደልም፤ማለት ግንቦት 7 የኢትዮ-ዲያስፖራ ሚዲያ ጠቅልል ነው። (G7 political organization is Ethio-diaspora Media maker VS notMedia Taker, as that of price maker trade monopolist VS price taker traders in free the market economy. Hence, G7 is the Ethio-diaspora media monopolist or Ethio-diaspora media version of Murdoch).

ግንቦት7 በዘርፈ ብዙ ዜና አውታሮቹ (via its plural/multi-media plat form )የሚጫወተውን በጣም ጠቃሚ ጸረ-ወያኔ ትግል እሰዮ የሚባል ቢሆንም፤ ግንቦት7 የራሱን ሚዲያ ሠሪ/ፈጣሪ ባይሆን ኖሮ ፦ያላደረገውን አደረኩ፣ያልደረሰበት ደረስኩ ፣ያልገደ ለውን  ገደልኩ ፣ያልማረከውን ማረኩ፣ያልተዋጋውን  ተዋጋሁ፣በስድስት ወር ግፋ ቢልም በዓመት ውስጥ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ነጻ አወጣለሁ፣የግንቦት 7 አባላት የሌሉበት ዓለምም ሆነ የኢትዮጵያ ምድር የለም ወዘተ ለማት አይችልምም አይደፍርምም ነበር ። የሌሎችን የጭንቅላት ምርት/ውጤት ማለት ጽሁፍ/ፎች ኮርዦ(by committing an act of plagiarism) የእኔ ነው ብሎ አድባባይ ማውጣት አይችልምም አይደፍርምም ነበር።

**የሌሎችን የጭንቅላት ምርት/ውጤት መኮረጅን(by act of committing plagiarism) በተመለከተ- ምሳሌ**

“የናዚ ጀርመንና የወያኔ ኢትዮጵያ ሲነጻጸር (Nazi Germany VS Woyane Ethiopia” በሚል አርእስት በ(Nov2,2o17) በግርማ ደገፋ በእሳት ቲቪ(ESAT TV)የቀርበውን ዘገባ ያዳመጣችሁ ወይም የተከታተላችሁ ፤ከዚኅ ዝቅ ብሎ ባለው አርእስትና ስም የተጻፈውን ጽሁፍ አንብቡ ፤ወይም ጽሁፉን ካንብባችሁ በኃላ ግርማ ደገፋ በእሳት ቲቪ ያቀረበውን ዘገባ አዳምጡ።

ከዚህ ዝቅ ብሎ በምታገኙት አርእስት የጻፍኩትን ጽሁፍ በወቅቱ ለተለያዩ የኅትመት ድረገጽ (print media) ልኬላቸው አደባባይ አውጥተውታል። የግንቦት7 ንብረት በሆነው በኢትዮጵያውያን ማኅበር/ኮምኒቲ ዲሞክራሲያዊ መድረክ (ECADF) ድረገጽም ወጥቷል። ግርማ ደገፋ “የታሪክ መጽሃፍት አገለባብጠን.....” ያጠናቀርነው በሚል፣የቃላት ስም/ቅቤ ቀባብቶ፣ በምስል አስደግፎ፣አስመስሎና ቅርጽ ስጥቶ ያቀረበው ጥንቅር **ይዘቱ የእኔ ጽሁፍ ነው ።**

**ማሳሰቢያ 1** - ከዚህ ዝቅ ብሎ የምታገኙትን ጽሁፌ አንባቢያንና ግርማ ደገፋ በእሳት ቴሌቭን (2November 2017) ያቀረበውን ዘገባ ለተከታተላችሁ፣ ለመከታተል አጋጣሚውን ያልገጠማችሁ ፣ነገር ግን የእኔን ጽሁፍ ስታነቡ አነጻጽራችሁ የኅሊና ሚዛን ለመስጥት ስትሉ የግርማ ደገፋን ዘገባ ማዳመጥ ለምትፈልጉ ሁሉ፡- አእምሮዋችሁን ሰብስባችሁ(mindful) ሆናችሁ **እንድታነጻጸሩ** በትኅትና የማሳስባችሁ/የምጠይቃችሁ ፤ **የእኔን ጽሁፍ አበይት/ምርግኩዝ ነጥቦችና የግርማ ደገፋን ጥንቅር ምርኩዝ ነጥቦችን ተመሳሳይ ወይም ተመሳሳይ መንትያ (identical twins) መሆናቸውን ነው ።** ስለናዚ-ጀርመኒ (Nazi-Germany) ከወያኔ ተግባር ጋር አነጻጽሬ ስጽፍ ከጥራዝ ነጠቅ እውቀት ተነስቼ አይደለም።ባለሁበት ባዕድ አገር በከፍተኛ የትምህርት መስክ ከተማርኳቸው የትምኅርት ዓይነቶች/አንዱ ነው።በጣም የምፈልጋቸውን ነጥቦችን መዝዤና አሳጥሬ ነው የጻፍኩት።

ሁላችንም እንድምናውቀው ከጋዜጠኝነት ሞያዎች አንዱ ከማኅበርስቡ/ኮምኒቲ አባል/አባላት የሚሰሙ ፣የሚነሱ፣የሚደመጡ ወዘተርፈ፡- ብሶቶች፣ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች ፣ተከታትሎ ና አጣርቶ የጉዳዩ/ጉዳዮቹ ውጤት ለባለጉዳዩ/ጉዳዮቹ ማድረስ ወይም አደባባ (public) ማውጣት ነው።ስለሆነም፡-

**ማሳሰቢያ 2፡-** በኢትዮ-ዲያስፖራ የሬዲዮ አገልግሎት ለምትሰጡ ፣በኢትዮ-ዲያስፖራ ፓልቶክ በሞዴረትነት ለምታገለግሉ ፣ በኢትዮ-ዲያስፖራ የውይይት መድረክ በመሪነት ለ ምታገለግሉ እና በኢትዮ-ዲያስፖራ ኅትመት ዜና አውታር (print media) በአዘጋጅነት ለምታገለግሉ ሃቀኛና ውድ ኢትዮጵያውያን! **ከዚህ ዝቅ ብሎ በሚገኙ አርእስትና ስም የተጻፈውን ጽሁፍ ሲደርሳችሁ ‘በነጠላም ሆነ በቡድን’ ግርማ ደገፋ ከላይ በተጠቀሰው ቀን**

በእሳት ቲቪ ካቀረበውን ጽሁፍ ጋር ያለውን ተመሳሳነት ፣ተቀራራቢነት እና ልዩነት፣ ሰነጣጥ ቃችሁ፣ ገምግማችሁና አነጻጸራችሁ እንድታዩልኝና ውጤቱን አደባባይ እንድታወጡልኝ በትኅትና አሳስባችኋለሁ ፤አቤቱታ አቀርባለሁ ።

ምክንያቱም ፡-

-የእኔ ጭንቅላት ምርት (intellectual property) ወሰደውብኛል ቢዬ ካመንኩ ወይም ከተጠራጠርኩ የመቃወም መብት እንዳለኝ ስለማውቅ

-አንዳንድ የኢትዮ-ዲያስፖራ የሚዲያ ባለቤቶችና የሚዲያ ሞያተኞች በማን-አለብኝነት (negligence) የሚሰሩትን ስህተት መፋለም/መቃወም ስለሚያስፈልግ፤ ነጻ ግልቤያ (free ride) መስጠት ስለማያስፈልግ

-እውነትን ለማስተማር (to keep the liars or the bastards honest)

-በከፍተኛ የትምህርት ገበታ በሚሰጡ በእያንዳንዱ አነስተኛም ሆነ ትልቅ 'ሐተታ ጽሁፍ' (minor or major essay) አንድም አንቀጽ ቢሆን ከጽሁፉን አርእስትና ሃሳብ ጋር ከተዛመዱ ጽሁፎችና ጸሃፊዮች እይታ ጋር ተደግፈው ወይም ተጣቅሰው ካልተጻፉ ጽሁፉ በአስተማሪዮች ተቀባይነት አይኖረውም። አንድ አጭር ጥቅስ እንኳን ያለ ማጣቀስ አይፈቀድም ። የዚህን አሰራር፣ ደንብና ሕግ በዚያ ጎዳና ያለፉ ሁሉ ያውቁታል ። ማለት- ከእገሌ/ልት የተወሰደ፣እገሌ/ልት እንዳለው/ችው፣ እንድ እገሌ/ሊት አባባል፣እገሌ/ሊት እንድተከራከረው/ችው ወዘተ..በሚል ። (ለምሳሌ) ካነበብኳቸው መጽሃፍት ከአንዱ የቀሰምኩትን፣ በጣም አጭር ጥቅስ በሌላ ወቅት የሐተታ ጽሁፍ(essay) ስጽፍ፣ ጥቅሱ ለጽሁፌ ይስማማ ስለነበረና መጽሃፉን ፈልጌ ስላጣሁት ሳላጣቅስ ፣ እንድ ኢ-አዋቂ (layman) ተጠቀምኩበት። በዚያ ምክንያት አስተማሪዬ የጥያቄ ምልክት አስቀምጦ ከማርኬ አምስት(5) ነጥብ ጎምዶ ሰጠኝ። ከዚህ በተጻራሪዩ (contrary to this);

_ ማንበብና መጻፍ የሚችሉ የዘመኑ ሰዎች ፡-ሳይለፉ ፣ሳይደክሙ፣መጽሃፍት ሳያገላብጡ፣እንቅልፍ ሳያጡ፣ ውጥረት (stress) ሳይሰማቸው ፣ሳይጨነቁና ሳይጠበቡ ወዘተርፈ በእውቀት ጥበብ (information technology) መሳርያነት/አማካኝነት ከሚፈሱትን ጽሁፎችና ሌሎች የእውቀት ዓይነቶች ኮርዠው ወይም ቆንጽለው የራሳቸውን የጭንቅላት ውጤት አስመስለው ሲጠቀሙ ይስተዋላል፣ ይታያል ፣ይደመጣል ።ከአገሬ ከተሰደድኩ ረዥም ዓመታት ስለሆነኝ፣ ኩረዠና ጥራዝ-ነጠቅነትን በተመለከተ ስለአሁኑ የአገር ቤቱ ትውልድም ሆነ ኢትዮጵያውያን ስላልሆነ ማኅበረሰብ አስተያየት መስጠት አልችል ። ነገር ግን በዲያስ ፖራው ዓለም ማንበብና መጻፍ ስለሚችሉ ኢትዮጵያውያን ኩረዠና ጥራዝ-ነጠቅነት ምን እንደሚሚስል ራሱን በቻለ ጽሁፍ እመለስበታለሁ ።

ወልዳብ ደንቡ

21 November 2017

ናዚ-ጀርመኒ ለ20ኛው መቶ ክ/ዘመን በጀርመን ሲነፃጸር ወያኔ/ህወሃት ለ21ኛው ክ/ዘመን በኢትዮጵያ

**ወልደአብ ደንቡ (12 ጄንዋሪ 2017)**

ጀርመን የተልያዩ ዘሮች(races) ፣ቋንቋዎች ፣ባህሎች ፣እምነቶች ፣ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ወዘተ..የነበራቸው ሰዎች እንድ አንድ ሕዝብ የሚኖሩባት አገር ነበረች ፤ ከ 1933 -1945 ዓ.ም ሂትለር የ**ፋሺዝምና የናዚዝም** የፖለቲካ ርዕዮቶችን መሥርቶና ተጠቅሞ -ጀርመንን ለመግዛትና ዓለምን በቁጥጥሩ ሥር የማድረግ ሙከራ ሲጀምር- መጀመርያ ያነጣጠረው የአርያን ደም(Arayan genetic make up) የላቸውም ወይም እነዚያ (the other) በሚላቸው ጀርመናውያን ላይ ነበር ።

ፋሺምና ናዚዝም- የአንድ ሳንቲም ፊትና ጀርባ ናቸው ፤ ሁለቱም አክራሪ ቀኝ ክንፍ የፖለቲካ ርዕዮቶች ናቸው( they are the two extreme right wing political ideologies) ።
**ፋሺም ከአክራሪ የቀኝ ክንፍ ብሄርተኝነት ይፈልቃል ፤ ማለት የፋሺዝም እናት አክራሪ ብሄርተኝነት ነው ።**

አክራሪ ብሄርተኝነት ሌሎችን ወይም እነዚያ (the other) የሚላቸውን ብሄር ብሄረሰብ አባሎችን ከፉኛ ይጠላል ። የሌሎችን -ቋንቋ ፣ባህል ፣ታሪክ ፣ማንነትና ሕልውና ይንቃል/ይረግጣል ፣ የራሱን የማንነት እሴቶች ያሳብጣል ፤ከማንም /ከምንም በላይ ነኝ ይላል ። የአክራሪ ብሄርተኛ የፖለቲካ ድርጀት አባሎች- የእነሱ ዘውግ ወይም ዘር ያልሆኑትን ሁሉ እንዲጠሉ ስለሚታነጹ - የስብዕና ንቃተ-ኅሊናና ሕዝባዊ ባህሪ ይጎላቸዋል - ስለሆነም የሌሎ ችን ብሶት፣ ሃዘንና መከራ አይጋሩም ፤ የእኛ አይደለም/አይደሉም በሚሉት/ሏዋቸው የሰው ልጅ/ልጆች ላይ የሚፈጸምን ግፍ አይሰማቸውም ፤ጨቋኝና ጨካኝ ናቸው ።

**በመሆኑም የጀርመን ፋሺዝምና ናዚዝም- ዋንኛ መርሃግብር (programme) ያተኮረው -በፀረ እነዚያ በሚላቸው ብሄረስብ አባሎች ወይም ዘሮች፣ በፀረ ይሁዳዎች (አንቲ ሰሜትዝም) እና የሌሎችን አገሮች በመውረር ላይ ነበር ።**

**ስለሆነም - የአርያን ዘር 'በተፍጥሮ የጠራ/ንጽህ ዘር' ነው ፤ በተፈጥሮ ከተበከሉ(polluted) ዘሮች ተለይቶና እርቆ መኖር አለበት - አርያኖች በሥነፍጥረት (በባዮሎጂ) ከሌሎች ዘሮች ከሚተላለፉ - ማንኛውም በሽታ ማጽዳት/መከላከል አለብን ፤ጀርመናዊ አርያን ሃያል ዘር ነው (Germanic Aryan race is master race) ስለሆነም ዓለምን መግዛት እንችላለን ወዘተ..በሚል ቅስቀሳና ፕሮፓጋ ዳ ምክንያት - ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው -ፖሊሽዎችን ፣ሩሲያዎችን፣ ዩክሬኒያዎችን፣ ስላቮችን፣ጥቁሮችን ፣ ጅፕሲዎችን፣ሰርብዎችን ፣ሮማኒያዎችን ፣አካለ ስንኩሎችን ወዘተ.. ያለፍርድ በጅምላ ጨፈጨፉ/መነጠሩ ። የሂትለር ቀኝ እጅ በነበረው- በአዶልፍ ሃይክማን (Adolf Eichman) አዛዥነት 6 ምሊዮን አይሁዶችን በመርዝ ጋዝ አፍነው ሸረከሟቸው ። ድርጊቱ ሆሎኮስት (Holocaust) በአይሁዳዎች ቋንቋ ሸወአህ(Shoah) በመባል ይታወቃል ።**

በ21ኛው መቶ ክ/ዘመን በኢትዮጵያ የተፈጠረው ናዚዝም ማለት የአክራሪ የቀኝ ክንፍ ብሄርተኛ **ወያኔ/ህወሃት በባንዳው መለስ ዜናዊ መሪነት-የፊንፍኔ** ቤተገዢዮችን አምባ በቁጥጥር ሥር ካዋለ ማግስት ጀምሮ -በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍና ደባ -ናዚዮች በጀርመን ሕዝብና በጀርመን ላይ ከፈጸሙት ግፍና ደባ የከፋ ነው ። እንዴት?


- ከአንድ ወንዝ ወይም የዘር ኩሬ(genome) የመነጨን ፣(አንድ ብሄራዊ) - ታሪክ ፣ ባህል ፣ ቋንቋ ፣ ሥነልቦና ፣ገድል ወዘተ.. ያለን ፤ ለበርካታ ሺ ዓመታት እንድ አንድ ሕዝብ የኖርን ኢትዮጵያውያን ፤ በጎሳ ቋንቋና በጎሳ ሥነልቦና ተሸንሽነን እንድንኖር ፣እንድንገዳደልና በጥላቻ ዓይን እንድንተያይ አድርገዋል
- ጀግኖች ጥንቶቻችን ፣ አያቶቻችንና አባቶቻችንን ለብዙ ሺ ዓመታት ያላስደፈሩትን - አገራዊና ሕዝባዊ ልዑላዊነታችን ፣የባህር በሮቻችን ፣ የመልካአ ምድራችን ዳርድንበሮች አስደፍሯል ፣አገር አስገንጥሎዋል ፣ ሕዝብ ከፋፍሎዋል ፣ የባህር በር አልባ አድርጎናል ፣መሬቷ ቆራርሶ ለጎረቤት አገርና ለሩቅ ባዕዳን ሸጠዋል ወዘተ ።

  የግብረ ሰናይነት **መተክልና የአገሮች ልዑላዊነትን ሕግ የጣስ ቢሆንም -የጀርመኑ ፋሽስቶችና ናዚዮች ጀርመንን ለማስፋፋትና ለማተለቅ ተዋጉ እንጂ-የጀርመንን ልዑላዊነት ለማስደፈር ፣ የጀርመንን ዳር ድንበር ለመቆራረስ/ለመሸንሸን ፣የጀርመንን የባህር በር ለማስወሰድ ፣የጀርመንን ብሄራዊ ቋንቋ ለማሳነስ ፣የጀርመንን ታሪካዊ ቅርሳ ቅርስ ለማጥፋት ወዘተ.. አልተነሱም ፣አልተዋጉም ፤ፖሊሲ አላወጡም ። በዚህ ምክንያት ነው - ወያኔ/ህወሃት ከጀርመን ፋሽስቶቻና ናዚዮች የከፋ ነው ያልኩት/የምለው ። አስተውሉ - ከእነዚህ ግዙፍ ከናዚዮች ታሪክና ለሃያ አምስት ዓመታት ደጋግመን ከሰማነው እኮይ/መሰሪ የወያኔ ታሪክ መቀንጨብ የፈለኩበት ምክንያት ፤ ላስተላልፈው ከፈለኩትን መልዕክት ጋር ስለሚዛመድ ብቻ ነው ( for being contextual with this article`s message**)
- ፋሽስቶችና ናዚዮች - የጀርመን አርያን ዘር በስነፍጥረት የጠራ/ንጹህ ዓለምን መግዛት የሚችል ሃያል ዘር (race) ነው እንዳሉ ሁሉ - መለስ ዜናዊ ትግሬ ወርቃማ ዘር ነው ፣ ከዚህ ከወርቃማ ዘር በመፈጠሬ እጅግ በጣም እኮራለሁ ብሎዋል ፤ ማለት ሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ ከብር ወይም ከነሃስ ስለተፈጠሩ ለእኛ ለትግሬዎች መገዛት አለባቸው ለማለት የተጠቀመበት ቋንቋ እንደሆነ ተረድተናል ። ሌሎች ቁንጮ የወያኔ ገዢዮቻችንም እኛ ትግርረዎች ካልገዛናት ኢትዮጵያ ተበታተናለች ማለታቸው የኢትዮጵያ ሃያል ዘር (Master race) እኛ ነን ማለታቸው እንደሆነ ይገባናል ።
- ፋሽስቶችና ናዚዮች - 6 ሚሊዮን አይሁዳዎችን እንድመነጠሩ ሁሉ ወያኔ ከ2-3 ሚሊዮን አማሮችን አጠፋ/መተረ

- ፋሽስቶችና ናዚዮች - ፖሊሽዎችን ፣ጅፕሲዎችን ፣ ሰርቦች ፣ጥቁሮችን ወዘተ..እንደጨፈጨፉ ሁሉ ወያኔ/ህወሃት - ኦሮሞችን ፣ጋምቤላዎችን ፣ኮንሶዎችን ፣ቤኒሽንጎዎችን ወልቃይቶችን ፣ቦረናዎችን ፣በቅርብ ግዜ የዲላ ነዋሪ ጉራጎችን ወዘተ..በጅምላ ጨፈጨፈ
- ናዚዮች የማይፈልጓቸውን ወይም እነዚያ የሚልዋቸውን ሰዎች የሥነዘር ፍሬ የማምከን ሳይንስ (**eugenism/eugenics**) እንድተጠቀሙ ሁሉ ***ወያኔ/ህወሃት*** በአማራ ብሄረሰብ እናቶች ላይ ***ዘርን ማምከኛ መርዝ ተጠቅሞዋል***
- ናዚዮች የጀርመን አጎራባች አገሮችና መላውን አውሮጳ እንደወረሩ ሁሉ -ወያኔ/ህወሃት የትግራይን ግዛት ለማስፋፋት/ለማተለቅ የትግራይ -አጎራባች ክ/ሃገሮችን ድንበር ጥሶ በጠመንጃ አፈሙዝ/ በሃይል - ከወሎ ፣ከጎንደር ፣ከአፋር ፣ከወልቃይት ከጋምቤላ ወዘተ.. ምርጥና ለም መሬቶች ወስዶ ወደ ትግራይ አካሎዋል ። የወያኔ/የህወሃት ምሥራቾችና የአሁኑ ገዢዮቻችን - በተግባራቸውና በሥነልቦና ፀረ-ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁኑ እንጂ በትውልድ (by birth) ኢትዮጵያውያን አይደሉም ብሎ የሚከራከር ያለ አይመስለኝም ። ወያኔ/ህወሃት ኢትዮጵያን ወረረ በማለት ስለሚነሱ - ክርክሮችና አመለካከቶች ከሚመስል የወረራ መስፈርቶች ወይም ማስረጃዎችጋር አጣጥሞ መጻፍ ስለሚያስፈልግ በሌላ ግዜ እመለስበታለሁ ።
- ገስታፖ ለፋሽስት/ናዚጀርመኒ = ካድሬ ለኢትዮ-ወያኔ ፤ ገስታፖ በመባል ይታወቁ/ይጠሩ የነበሩት ፀረ- ሕዝብ የፖለቲካ ሰላይ ፖሊሶች ፤ (1) የጀርመን ሕዝብ - የሚያወራውን ፣ የሚያደርገውን ፣ የሚያስበውን ፣የሚበላውን ፣ የሚጠጣውን ወዘተ.. በመሰለል (2) በፖለቲካና በሲቪክ ተቃዋሚ ድርጅቶች ውስጥ ሰርገው በመግባትና በገሃድ በማዳከም እና የጀርመንን ፋሽስታዊ ሥርዓት ዕድሜ ለማራዘም ቁልፍ ሚና ተጫውቷል ። ሁላችንም እንደምናውቀው አንድ ለአምስት የተደራጁትን ፀረ-ሕዝብ የወያኔ/ህወሃት ካድሬዎችም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የገስታፖዎች ሚና ተጫውቷል እየተጫወቱም ነው ፤ የአንድ የጋለ ምጣድ ፊትና ጀርባ ናቸው ።
- ኤሰ ኤስ (SS) ለናዚ ጀርመኒ = አጋዚና የፈደራል ፖሊሶች ለኢትዮ-ወያኔ ፤ SS(Corps of Nazi party)ማለት ነው ። የገፍና የግፍ ግዲያ እንደ ሆሎከስት (Holocaust) ዓይነቱ ፣ ሕዝባዊ አመጽ የማፈን የገፍ እሥር ቤቶች/ኮንሴትሬሽን ካምፕ የማስተዳደር ፣ የዘረኝነት ፖሊሲ ወይም መመርያ የማስፈፀሚያ ወዘተ.. መሣሪያ ነበሩ ።አጋዚና የፌደራል ፖሊስ ተብዮች ከሞላ ጎደል ተመሣሳይ ሥራ ነው የሚሰሩት
- ሶንደርገሪችት (Sondergricht) ለናዚ-ጀርመኒ = ለኢትዮ-ወያኔ ፍርድ ቤት ፤ በጀርመኖች ቋንቋ ሶንደርገሪችት ማለት- የሕዝብ ፍርድ ቤት (the people`s court) ማለት ነው ። የናዚ ጀርመኒ ፍርድ ቤቶች - ፕሬዝዴንቶችና ዳኞች ለሞትም ሆነ ለእሥር ቅጣት ሲፈርዱ የጀርመንን የዳኝነት ሕገ-መንግሥት ህግ ተከትለው ሳይሆን የናዚ ፓርቲ በሚሰጣቸው መመርያና ትእዛዝ ነበር ። በተመሳሳይ የዘመነ ወያኔ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዳኛ ተብዮችም በዜጎች ላይ የሚፈርዱት - የፍትህን መተከል ወይም መርህ ተከትለው

ሳይሆን -የወያኔ/ህወሃት ፓርቲ ሹሞች በሚሰጥዋቸው ትእዛዝ ነው ። ሁለቱም የካንጋሮ ፍርድ ቤት ተምሳሊት ናቸው ። የካንጋሮ ፍርድ ቤት (kangaroo court) ከአሜሪካ /ኢ-ይፋዊ እንግሊዝኛ (illiterary English) የመነጨ ሲሆን - (የቀልድ ፣የይስሙላ ፣ የፍርደ-ገምድል ፣ የኢ-ፍትህ ፣ የሩጫ ፣ የጭካኔ ፣ የአድሎ ፣ የበዘፈቀድ ፣ ቅንነት የጎደለው ወዘተ...ፍርድ የሚሰጥበት ፍርድ ቤት እንደማለት ነው) ።

- ሂትለር የጀርመን ቻንስለር በመሆን ለከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣን የበቃው እ.አ.አበ1933ዓ.ም ነው ። የዚያን ጊዜ ጀርመን የዊመር ሪፐብሊክ (The Weimer Republic)በመባል ይጠራ ነበር ። የጅርመን ብሄራዊ ባንድራ/ፍላግ - ከጥቁር፣ከቀይና ከወርቃማ ብጫ ቀለሞች የተሠራ ነበር ። .........ከ 1935 -1945 ዓ.ም የጀርመን ባንድራ በስዋስቲካ(Swastika) ማለት ከዚህ ዝቅ ብሎ በሚታየው ምልክት ተተካ ።የምልክቱ ትርጉም' መልካም ዕድል/good luck' የሚል ሲሆን - በቃላት ለመግለጽ ሚያስቸግር መዓት/ቁጣ አስከትልዋል ።



**በተመሳሳይ፥ የ21ኛው መቶ ክ/ዘመን የኢትዮጵያው ፋሽስት-ናዚ ማለት ወያኔ/ህወሃት ከሁሉም አገራት ባንድራዎች ቀደምትነት ያለው መሆኑን የሚታወቀው ፤ቢያንስ እ.አ.አ ከ1900 ዓ.ም ጅምሮ ማለት እ.አ.አ ሰኔ (June) 28/1919 ከተመሰረ ተው (League of Nations) በመባል ከሚታወቀው - የያኔ የዓለም መንግሥታት ድርጅት ከመመስረቱ በፊት -እውቅና ያገኘው 'ሰንደቅ ዓላማችንን የመቶ ዓመት ታሪክ ያለው አገር የሚወክ**

ል ጨርቅ በመሆኑ ወያኔ/ህወሃት ለሚገዛው ኢትዮጵያ አይወክልም በማለት በምትኩ የሰይጣናዊ መንፈስ እምነት (satanic cult) ተከታዮችን ምልክት/ሲምቦል በሆነው - ባንድራ ተካው (ወያኔ/ህወሃት) ፤ ባንድራ የጣሊያን ስም መሆኑን ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል ፤ እዚጋ ባንድራ ስል ወያኔ ሆኜ መናገሬ ነው ።

ለ 25 ዓመታት ዓይተነው ዓይተነው የሰለቸን ስለሆነ - ምስሉን እዚህ ጋ መለጠፉ አልፈለኩም ። **Satanic cult ritual (SRA), sometimes known as ritual abuse, ritualistic abuse, organised abuse, sadistic ritual abuse and other variants) was the subject of a moral panic that originated in the United States in the 1980s; spreading throughout the country and eventually to many parts of the world by the late 1990s** *https://en https://en.wikipedia.org/wiki/**Satanic**/* ግልጽ እንግሊዝኛ ስለሆነ ወደ አማርኛ መተርጎም አልፈለኩም ።
ወያኔዎችም ጫካ እያሉ በሚሠርዋቸው -ተንኮሎች ፣ በሚፈጽሟቸውን ግፎች ፣ባፈሰሱት የሰው ደም ወዘተ... ሲሸበሩና ሲደናገጡ - ለሰይጣናዊ ለ(satanic cult) እምነት የሆነው ምስል/symbol ይማጸኑ ነበር ማለት ነው ። ስለሆነም ቀንቷቸው የፖሊቲካ ስልጣን ሲጨብጡ ባንድራቸ ው አደረጉት ማለት ነው ።ይህንን አስመ ልክቶ በርካታ አተያይ/ቪዩ ማስቀመጥ የሚቻል ቢሆንም ፤ አንባቢ ላለማስልቸትና ጊዜ ከመቆጠብ አንጻር ማሳጠሩን መርጥኩ ።

- አዶልፍ ሂትለር ነገደ እስራዔሎችን ከጠላበት አሥር (10) ምክንያቶች አንዱ - በዋናነት በንግድ ላይ ተሠማርተው በጀርመን የኢኮኖሚዩን ዘርፍ ትልቁን ድርሻ በመያዛቸው፣ ሃብታም በመሆናቸውና - ይህዳውያን ከአርያኖች የተሻል ኑሮ በመንራቸው ቀንተው ባቸው ነው ይላሉ ታሪክ ፀሃፊዮች ። በተመሳሳይ ህወሃት የኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥ ት በያዘ ማግሥት - ፖለቲካውን ከአማራ የንግዱን ዘርፍ ከጉራጌ መንጠቅ ቀደምት ዓላማው እንድሆነ አወጀ ።
  በዲሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት ሥርዓት - በዜግነት ፖለቲካ ለሥልጣን መወዳደር በማይቻልባቸው ፤ በጠመንጃ አፈሙዝ የፖለቲካውን ሥልጣን በአምባገነን ንጉሣዊ (absolute monarchy) ሥርዓት ፣ ህዳጣን ብሄር /ብሄረሰቦች እና ወታደራዊ መንግ ሥት በሚፈራረቁበት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች - ከፖልቲካ ሥልጣን የተገለሉ ወይ ም እዚያ መድረስ የማይችሉ የአናሳ ብሄረሰበ አባሎች - በንግድና በተራ ሥራ ዘርፍች እንድሚሠማሩ ከአንዳንድ ግራ ዘመም የፖለቲካ ሳይንስ መፅሃፍት መማር ይቻላል ።
  በመሆኑም አሁን እስከ ደረስንበት 21ኛው መቶ ክ/ዘመን - የጉራጌ ብሄረሰብ የጠመንጃ አፈሙዝ ተጠቅሞ ለፖለቲካ ሥልጣን ከማይወዳደሩ አናሳ ብሄረሰቦች አንዱ ለመሆኑ

ምስክሩ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ። ምክንያቱ/መነሻው ለምን እንድሆነ ባይታወ ቅም - የጉራጌ ብሄረስብ ሥራ ወዳድነት ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሁሉ የተለየ ስለመሆኑ እዚህ ጋ መግለጽ ለቀባሪ መርዶ ማርዳት ይሆንብኛል ፤ "necessity is the mother of invention" ማለት ችግር ብልሃት ያስተምራል ስለሆነ ይሆን ? "Labour created man himself" (Frederick Engels) ማለት 'ሰውን ሰው ያደረገው ሥራው ነው' የተሰኘው (የፌደሪክ ኤንጅልስን) ጥቅስ ወይም መርህ የሥራ ባህላቸው ያደረጉት ፈሬደሪክ ኤንግልስ ገና ሳይወለድ ነው ።

ከጫማ ጠራጊነት አንስቶ በየትኛውም ዝቅተኛ የሥራ ዘርፎች ተሠማርተው በመስራት - የሥራ ክቡርነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተምረዋል ። ከተሰማሩባቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ ነግደው የመኖር ዘርፍ ሲሆን - ከሱቅበደረቴነት ንግድ እስከ አስመጪና ላኪ (exporters and importers) ለመሆን በቅቷል ። በቅድመ ወያኔ/ህወ ሃት በኢትዮጵያውያን የሃብት አሰላለፍ በርካታ ጉራጌዎች - የኢትዮጵያ ብሄራዊ ከበርቴ ለመሆን በቅተው ነበር ። አሁን ግን እንኳንስ የኢትዮጵያ የአንድ መንደር ከበርቴ የሆነ ጉራጌ የለም ።
ሂትለር አይሁዶዎችን ከጠላበት ምክንያቶች አንዱ ሃብታም በመሆናቸው ቀንቶባቸው እንድ ነበረ ከላይ ጠቅሼአለሁ ።ወያኔ/ህወሃት ጉራጌዎች የጠላበት ምክንያቶች ሁለት ናቸው ። (1) በንግዱን ዘርፍ ቀንና ለሊት ሠርተው - በሃብት ከሌሎች ብሄረሰቦች በልጠው በመገኘታቸው ቀንቶባቸው ነው ። ጉራጌዎችን በንግዱ መሥክ የነበራቸውን የበላይነት ለማዳከምና ከዚያ ለማፈናቀል ፤ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ -ግብሮች፣ ቀረጦ ችና የባንክ ወለዶች ጫነባቸው ። የማይችሉትን የቤት ክራይ በማስከፈል ለንግድ ምቹ ከሆኑ ቁልፍ ቁልፍ መናኸርያዎች አፈናቀላቸው ፤ በሱቅበደሬተነት - ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ይነግዱ የነበሩትንም እነሱን ለማባረር በተመደቡትን ፖሊሶች -በየእለቱ ይደርሥባቸው በነበረው የዱላ ድብደባ ተማርረው - ወደ ለምኖ የመኖር ሕይወት ተሰማሩ ።
ህወሃት የጉራጌ ነጋዴዎችና ቤተሰባቸው ሰብስቦ እንደ ሂትለር መርዛማ ጋዝ አሳጥኖ ባይፈጃቸውም - በረሃብ ፣በድኅነትና በእነዚህ ምክንያቶች በሚመጡ በሽታዎች በቀስ በቀስ ወይም ባዝጋሚ ሞት እንዲያልቁ አደረገ ። የንግዱን ዘርፍ - በህወሃት የንግድ ተቋ ም ፣የህወሃት የፕለቲካ አቅም በሚያጠናከሩ ትውልደ ትግራይ በሆኑትን ኩባኒያዎች ፣ ቡድኖች ፣ግለሰዎችና ካድሬዎች ተተካ (2) ህወሃት ጉራጌዎችን የጠላበት ሁለተኛው ምክንያት -አማራን ወግነው ፀረ-ህወሃት አቋም አላቸው በሚል ነው ። አዎን ወያኔ የኢ ትዮጵያ ሕዝብ በጎሣ ክልል ሸንሽኖ ማስተዳደርን አስመልክቶ ጉራጌዎች ቶሎ አሚን እንዳላሉትና እንደተፋለሙት በአንድ መጽሄት ተጽፎ አንብቤያለሁ ፤ "ከሰሜን የአገራ ችን ጫፍ እስከ ደቡብ የአገራችን ጫፍ ፤ ከምሥራቅ የአገራችን ጫፍ እስከ ምዕራብ የአገራችን ጫፍ ተዘዋውረን መኖርና መሥራት በትውልድ ዜግነት ያገኘነው መብታች"

ነው የሚል ሙግት እንድገጠሙት ለግዜው ስሙን በረሳሁት አንድ የአማርኛ መጽሄት ውስጥ አንብቤያለሁ ።
ሂትለር የሃያላን ምዕራብ መንግሥታት አገሮች ማለት ታላቋ እንግሊዝ ፣ ፈራንሳይና የሶቭየት ኅብረትን በመውረሩና የእነዚህን አገሮችና የአሜሪካ - የኢኮኖሚ ጥቅሞች ለመሻማት በመዳፈሩ ፋሽስት አሉት እንጂ ፤ ሂትለር በጀርመኒና በጀርመን ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግፍ- ወያኔ/ህወሃት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፈጸመው ግፍ በልጦ አይደለም ። ወያኔ/ህወሃት በእነዚህ ሃያላን መንግሥታት ጫማ ሥር በመውደቁ ና ለእነሱ ጥቅም የሚገለባበጥ በመሆኑ ፣ መቶ ምሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢግል/ቢጨፈጭፍ ፋሽስት አይሉትም ።

ወልደአብ ደንቡ